# <u>ያልተሰጠን፡ መንፈስ - ፍረሃት</u>

በቅርቡ፡ የኢትዮጵያው፡ ጠቅላይ፡ ሚኒስቴር፡ ከታይም፡ ጋር፡ ባደረጉት፡ ቃለ-ምልልስ፡ “ሌሊት፡ እንቅልፍ፡ የሚነሳዎት፡ ምንድን፡ ነው?” — (“What keeps you awake at night?”) ተብለው፡ ሲጠየቁ፡ “ሁልጊዜም፡ ፍረሐት፡ ነው።” — (“It has always been fear”) በማለት፡ መልሰው፡ ስለ፡ ሃገር፡ ያላቸውን፡ ስጋትና፡ ተስፋ፡ መተንተን፡ ይቀጥላሉ። በርግጥ፡ ገጣሚው፡ ዮሐንስ፡ አድማሱ፡ “ፍረሃት፡ የኛ፡ ጌታ” በሚል፡ ርዕስ፤

“ፍረሃት፡ የገዛን፡ እኛ፡ የፍረሃት፡ ሃገር፡ ዜጋ፣

በፍረሃት፡ ብቻ፡ መቸም፡ መውጫ፡ መግቢያችን፡ የተዘጋ”

በማለት፡ እንደተቀኘው፡ ፍረሃት፡ የሁሉ፡ ጌታ፡ ነው። ነገስታቱን፣ ተራውን፤ ኃብታሙን፣ ደሃውን፤ ትንሹን፣ ትልቁን … ያሸብራል። ባለንበትም፡ አሜሪካ፡ ፍረሃት፡ በብዙ፡ መልኩ፡ የሰዎችን፡ ሕይወት፡ ይቆጣጠራል። ሰዎች፡ ስለ፡ ስራ፡ ዋስትና፡ ይሰጋሉ፤ ሽብርተኞች፡ ምን፡ ያደርጉ፡ ይሆን፡ ሲሉ፡ ይፈራሉ። ስለ፡ ጤንነትና፡ ወንጀል፡ ይጨነቃሉ። የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ግን፡ በክርስቶስ፡ ኢየሱስ፡ አምነው፡ ስለዳንቱ፡ ሲናገር፡ የኃይል፡ የፍቅርና፡ እራስን፡ የመግዛት፡ መንፈስ፡ እንጂ፡ የፈረሃት፡ መንፈስ፡ አልተሰጠነም፡ ይላል።

ፍረሃት፡ የእምነት፡ ተቃራኒ፡ ነው። ለዚህ፡ ነው፡ መጽሐፍ፡ “እመን፡ ብቻ፡ እንጂ፡ አትፍራ” የሚለው (ማርቆስ 5፡36)። በእግዚአብሔር፡ የሚታመን፡ ሰው፡ ነገ፡ ምን፡ እሆናለሁ፡ ብሎ፡ አይፈራም። ይልቁንም፡ ጻድቅ፡ በእምነት፡ በህይወት፡ ይኖራል፡ ተብሎ፡ እንደተጻፈ፡ እያንዳንዱን፡ ቀን፡ በእግዚአብሔር፡ ላይ፡ በማረፍ፡ ይኖራል። እግዚአብሔር፡ በፍረሃት፡ እንድንጨመደድ፡ አይፈልግም። ምክነያቱም፡ በመጀመሪያ፡ ፍረሃት፡ ከሃጢያት፡ ጋር፡ የገባ፡ ነው። አዳም፡ በሃጢያት፡ በወደቀ፡ ጊዜ፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ፈርቶ፡ ተሸሸገ። ከሃጢያት፡ ልምምድ፡ በፊት፡ አዳም፡ ፍረሃት፡ አያውቅም፡ ነበር። ሃጢያት፡ ትእዛዝን፡ በመተላለፍ፡ ከገባ፡ በኋላ፡ ግን፡ ፍረሃትም፡ ከሃጢያት፡ ጋር፡ ገባ። ስለዚህ፡ መጽሐፍ፡ ሲናገር “ኀጥእ፡ ማንም፡ ሳያሳድደው፡ ይሸሻል፤ ጻድቅ፡ ግን፡ እንደ፡ አንበሳ፡ ያለ፡ ፍርሃት፡ ይኖራል።” ይላል (ምሳሌ 28፡1)። ሃጢያት፡ ሰውን፡ ፈሪ፡ የሚያደርገው፡ በሰውና፡ በእግዚአብሔር፡ መካከል፡ ባለው፡ ግንኙነት፡ ስለሚገባ፡ ነው። ስለሆነም፡ የፍረሃት፡ ማርከሻው፡ አዳም፡ እንዳደረገው፡ ከእግዚአብሔር፡ ፊት፡ መሸሽ፡ ሳይሆን፡ ወደ፡ እርሱ፡ መቅረብ፡ ነው። ያን፡ ጊዜ፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አማካኝነት፡ የእግዚአብሔር፡ ኃይል፣ ፍቅር፣ ሰላም… ወደ፡ ልባችን፡ ይፈሳል። የእግዚአብሔር፡ ኃይልና፡ ፍቅር፡ ባለበት፡ ደግሞ፡ ፍረሃት፡ ሊኖር፡ አይችልም። ምክነያቱም፡ መጽሐፍ፡ እንደሚል፡ ፍጹም፡ ፍቅር፡ ፍረሃትን፡ አውጥቶ፡ ይጥላልና።

እግዚአብሔር፡ ልክ፡ ፈረስ፡ “በፍረሃት፡ ላይ፡ ይስቀል” (ኢዮብ 39፡22) እንደተባለ፡ እኛም፡ ልጆቹ፡ በፍረሃት፡ ላይ፡ እንድንስቅ፡ ይፈልጋል። እስቲ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ኢያሱን፡ እንዴት፡ እንዳበረታታው፡ ተመልከቱ። “በምትሄድበት፡ ሁሉ፡ አምላክህ፡ እግዚአብሔር፡ ከአንተ፡ ጋር፡ ነውና፡ ጽና፥ አይዞህ፤ አትፍራ፥ አትደንግጥ፡ ብዬ፡ አላዘዝሁህምን?” (ኢያሱ 1፡19)። ወገኖቼ፡ “ጽና፥ አይዞህ፡ አትፍራ፥ አትደንግጥ” የሚለው፡ ትእዛዝ፡ ዛሬም፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ በኩል፡ ወደ፡ እኛ፡ ደርሷል። ላለመፍራት፣ ላለመደንገጥ፡ በቂ፡ ምክንያት፡ አለን። ያም፡ የሰራዊት፡ ጌታ፣ ሁሉን፡ ቻይ፡ የሆነው፣ አልፋና፡ ኦሜጋ፡ እግዚአብሔር፡ ከኛ፡ ጋር፡ የመሆኑ፡ ጉዳይ፡ ነው። እግዚአብሔር፡ ከኛ፡ ጋር፡ ከሆነ፡ ምን፡ ያስፈራናል? ቃሉ፡ እንደሚል፡ “እርሱ፡ ከአዳኝ፡ ወጥመድ፡ ከሚያስደነግጥም፡ ነገር፡ ያድንሃልና። በላባዎቹ፡ ይጋርድሃል፥ በክንፎቹም፡ በታች፡ ትተማመናለህ፤ እውነት፡ እንደ፡ ጋሻ፡ ይከብብሃል። ከሌሊት፡ ግርማ፥ በቀን፡ ከሚበርር፡ ፍላጻ፥ በጨለማ፡ ከሚሄድ ክፉ፡ ነገር፥ ከአደጋና፡ ከቀትር፡ ጋኔን፡ አትፈራም። (መዝሙር 91፥ 3-6)። ወገኖቼ፡ የተሰጠን፡ መንፈስ፡ ሃይለኛ፡ መንፈስ፡ ነው። ከዚህ፡ መንፈስ፡ ጋር፡ ፍረሃት፡ ሊዳበል፡ አይችልም።